# አባ ፋኑኤል አዲስ ተክል ናቸው

ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ

nigatuasteraye@gmail.com

መጋቢት ፭ ፳፻፮ ዓ.ም.

"ወኢይኩን ተክለ ሐዲሰ ከመ ኢይትዐበይ ወኢይደቅ ውስተ ፍትሀ ዲያብሎስ። (፩ኛ ጢ. ፫፡፮) የክርስቶስን ትህትና ጠልቆ ያልተረዳ ክርስቲያን በዲያብሎስ ትእቢት ይሸነፋልና በመንፈሳዊ አመራር ላይ አታስቀምጥ።" አዲስ ተክል ማለት አዲስ ገና ያልበሰለ አማኝ ማለት ነው።

## መግቢያ

አባ ፋኑኤል ባዲስ ተክልነታቸው ነቢዩ ኢሳይያስ ስለ ጾም ከተናገረበት ምዕራፍ አንዲትን ሀረግ በጥሰው፣ በምእመናን እና በሶስት ቀሳውስት በቀድሞው ቄስ ታደሰ ሲሳይ ላይ የተላለፈውን ቃለ ውግዘት በቀላጤ ለማንሳት ባደረጉት ሙከራ "የከሳሾች ካህናት ጥላቻ ችግርና አለማመን ከዚህ ላይ ይጀምራል" በማለት የጻፉት ወረቀት ህዝቡን እንዳያደናብር ይህችን ጽሁፍ በማዘጋጀት ላይ ሳለሁ፣ ይሄይስ አእምሮ የተባሉ ወገን "የሃይማኖት እርጅና አያድርስ" በሚል ርእስ March 9/ 20014 የጻፉትን መልእክት ሁለት ወዳጆቼ ላኩልኝ።

የጽሑፉ ርእስ በግንባር ቀደም በምናገለግል ሰዎች ላይ የሚታዩብንን ስህተቶች አጉልታ በማሳየቷ ሳበችኝ። ጸሐፊው "ይህችን ጽሁፍ ባልጽፍ በወደድኩ ። ግን ያበጠው ይፈንዳ እንጅ እጽፋታለሁ። በስንቱ ታፍኘ እዘልቀዋለሁ። ብዙ ሚዲያዎች እንደማይቀበሉ ከወዲሁ አምናለሁ። በዚሁ ብቻ ከማሩኝ እሰየው ነው። ትልቅ እድለኝነት" በማለት ጽሁፏን ጀምረዋል። አባቶች "ከባህር ርጡብ ጢስ፣ ከየብስ ይቡስ ጢስ ተነስተው በአየር ላይ ሲገናኙ ነጎድጓድ ይከሰታል" ብለው የሚገልጹትን ነጎድጓድ መስላ ታየችኝ። ክፍርሀትና ከድፍረት ስሜት የተፈለቀች መልእክት ናት ለማለት ነው።

በወንድማችን አዕምሮ ውስጥ ሲጠራቀም የኖረውን ትዝብት ተሸክማ ብልጭ ያለችው ይህች ጽሁፍ፣ ወፈ ገዝቶች አስመሳይ ቀሳውስት በሰሩት ስህተት ላይ ብቻ አተኩራለች። ሀላፊነታቸውን እየተወጡ ካለፉት ቀሳውስት አንድ እንኳ ባለመጥቀሷ ቅር ቢለኝም፣ በቤተ ክርስቲያኒቱ ላይ የተሰነዘረ ነቀፋ ባለመኖሩ ደስ አለኝ። በሌላ በኩል ደግሞ ቤተ ክርስቲያናችን የህዝቡን አንድነት ስታንጽባቸው የኖረችባቸውን በዓለት ፋይዳና ጥቅም እንዳልነበረው አድርጋ በመግለጿ፣ አንድነታችንን እያፈረሱ የመጡት እነ አቶ ስብሀት ነጋ "ቤተ ክርስቲያኗ ለረዥም ዘመናት በማህበር በዝክርና በአመት በአላት በክርስትና ያንድነትን መንፈስ በህዝቡ አዕምሮ ላይ ስትተቀርጸው የኖረችውን ብሄራዊ የኢትዮጵያነትን ስሜት ከትግራይ ህዝብ አዕምሮ ጠራርጎ በጠባቡ ትግሬአዊነት ስሜት በመተካት የቤተ ክርስቲያኒቱን ይዘት እያጠበቡ ራሷን ቤተ ክርስቲያኒቱን መምታት ነው" ከሚለው መርኋቸው ጋራ ጽሑፏ የተሸከመችው ሀሳብ እጅግ በጣም ተቀራረበብኝ።

ከነ አቶ ስብሀት አፍራሽ መመሪያ ላለመጋራት በመጠንቀቅ ከDENOMINATIONAL INTEREST በራቀ መንፈስ ጠቃሚውንና ዘላቂውን ነገር ሳይመታ፣ ጎጅውን ብቻ ለይቶ በጥንቃቄ የሚቀርብ ነቀፋና ትችት ይበል ተብሎ ሊቀበሉት የሚገባ እንጅ የሚያስነቅፍ አይደለም።

ያለፈውን ስህተት መቃኘቱ እኛ እንዳንደግመው እና የራሳችንንም ስህተት እንዳንከምርበት ለማስጠንቀቅ ከሆነ መልካም ነው። ደርግ ራሱ ይሰራው የነበረውን ስህተት ለመሸፈን ከሱ በፊት በነበሩት መሪዎች ላይ እያጓነ በሚያቀርበው የክስ ጫጫታ፤ ወያኔም ኢትዮጵያን ወደብ አልባ ዜጎቻችችንም መንደር አልባ እያደረገ የሚፈጽመውን በደል ለመሸፈን፤ በደርግ ላይ እንደሚፈጥረው ጫጫታ፤ እያንዳንዳችንም በቀደሙ አባቶቻችን ላይ በምናስነሳው ክስ የየራሳችን ስህተት ወደ መሸፈኑ እንዳናዘነብልና፤ በሙት ወቃሽነትም እንዳንከሰስ የቅዱስ አትናቴወስን ፈለግ መከተሉ የሚጠቅም ይመስለኛል።

ቅዱስ አትናቴወስ እንደ ይሄይስ አዕምሮ ባለፉት ሰዎች ላይ የተሰማውን ምሬትና ቅሬታ ”ኦ አዳም ምንተኑ ረሰይናከ ዘአምጸከ ፍትሀ ሞት ላእሌነ። ኦ ሄዋን ምንተኑ ረሰይናኪ ናሁ ጸልመ ሥጋነ በብዝሀ ሀጣውእ ዘእምነበርነ በአርያ ሰማያውያን። ናሁ ይበክያ ኩሎን አዋልድኪ ሶበ ይወልዳ በጻእር ወህማም፤ ወይዴምዋ በከመ አድመውኪያ ለእንትኩ እጽ ዘውስተ ገነት።” እያለ ተናገረ። ማለትም :-“አባታችን አዳም ሆይ! የሞት ፍርድ ያመጣብንን በደል ያደረክ ምን በደልንህ? እናታችን ሄዋንስ ምን በደልንሽ ? በሰማያዊ ደስት እንዳንኖር አንች ባመጣሽው ስህተት ሰውነታችን ሁሉ ጠቆረ።” ይልና በመቀጠል፤ “ወንህነሰ እለ አመነ በዋህድ ወልድክሙ በአማን ንህነ አርአያክሙ ወአምሳሊክሙ እለ ወጻእነ እምሀቄክሙ። . . . . ኦ አዳም ወሄዋን እስመ አኮ ዘይትከሀል ኪያክሙ ንጽአል። በከመ ለልሳን ዘዕይትከሀል ንጽአልዎ እንዘ ይትናገሩ ቦቱ። ወከማሁ አንትሙ ንህነ ወንህነ አንትሙ።(ገጽ 218 ከቁጥር 28 _31” ማለትም:- “አባታችን አዳም እናታችን ሄዋን ሆይ! እኛ ልንጠላችሁ፤ ልንከሳችሁና ልንወቅሳችሁ እንችል ዘንድ እኛ እነማን ነን? እናንተም እኛ ናችሁ። እኛም እናንተን ነን።” ብሎ ደመደመደው።

የኛ እናትና አባቶችም ከአዳምና ከሄዋን የፈለቁ ናቸውና ፍጹማን ባለመሆናቸው ከነሱ የተላለፈብን የስህተት እርሾ ሊኖር ይችላል። በእጅጉ መወቀስና መከሰስ ያለብን ዘመናችንን መዋጀት ያልቻልን <u>ጣራና ግርግዳው በላያችን ላይ የፈረሰብን በዚህ ዘመን ያለን ደካሞች ቀሳውስት ነን</u>። በተለያዩ ጎሳዎችና ዘመናት የነበሩት ቀሳውስት ያሳዩትን ድካምና ብርታት በ (Anthoropological & sociological point of views) ለማየት ካልሞከርን በቀር፤ ባንዳንድ ሰብሮ ገብ አስመሳይ ቄሶች ብቻ ሁሉንም የምንለካቸው ከሆነ፤ ካንድ ዶሮ አካል ላይ፡ አንዷት ላባ ነቅሎ፡ ዶሮዋ ይህች ናት እንደማለት ይሆናል ብየ እሰጋለሁ። በሚሊዮን የሚቆጠር ህዝብ ይዛ ስትጓዝ በኖረችው በቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ በነበሩት ቀሳውስት አባቶቻችን ላይ ድካም እየፈለግን እምንናገር ከሆነ፤ እባብና ሄዋን ከአዳም ጋራ በተደመሩ ጊዜና ቦታ በገነት ውስጥ ስህተት መከሰቱን መርሳት አይኖርብንም። ከኛ በፊት የነበሩ አባቶቻችን ቀሳውስት እና እኛም እያወቅን በድፍረት፤ ሳናውቅ በስህተት በፈጸምናቸው በደሎች ይቅር በሉን እያልን በወሰድነው እርምጃ የምንወቀስ ከሆነ ቤተ ክርስቲያንን ጥላችሁ ውጡ ማለት ይመስላል። በቀድሞው ቄስ ታደሰ ላይ በወሰድነው ርምጃ “ወፈ ገዝቶች ያሰኛቸዋል አያሰኛቸውም” በሚለው መዝኑን እያልን በምንጮህበት ጊዜ ደርቦ ለመምታት መሞከር የሚጠቅም አይመስለኝም።

ከዚህ ሁሉ ይልቅ “የሃይማኖቱ መምህራን፤ ኦሪትን ከሀዲስ፤ ሰይጣንን ከእግዚአብሄር፤ እውነቱን ከሀሰት፤ ልማዳዊውን ከእውነተኛው የክርስቶስ አስተምህሮ በመለየት ህዝቡን በትክክለኛ መንገድ ቢመሩት የመጀመሪያ ተጠቃሚዎች እነርሱ መሆናቸውን ብጠቁም የሚያስነውር አይመስለኝም” ብለው የሰጡትን ምክር ተቀብየዋለሁ። ለሚመስሉኝ ቀሳውስትም ይህን ምክር እንስማ፤ መስማት ካልቻልን በቀድሞው ቄስ ታደሰ ላይ የወሰድነውን ርምጅ ወደራሳችን በማዞር ቅስናችንን እየተውን ከመቅደስ እንውጣ እላለሁ።

ሆኖም፤ በይሄይስ አዕምሮ የተነሱት ወቀሳዎች በደርግ ዘመን ተደጋግመው ተገልጸዋል። <u>የአቡነ ቴዎፍሎስ በሰማእትነት መሞታቸው ያላረካው፤ በደብረ ይድራስ እንደ ተረጨው እንደ ቅዱስ ጊዮርጊስ አጽም ያቡነ ቴዎፍሎስ ሰውነት ተፈጭቶ ባዲስ አበባ አድባራት ይረጭ የሚል መንፈስ ካልሆነ በቀር፤ በግፍ ለተገደሉት ለአቡነ ቴዎፍሎስ ሰማእትነት አይገባቸውም ብንል እንኳ፤ በጆሯችን ሰምተን ባይናችን ያየነው የሚወቀሱበት ስህተት ቢኖርባቸውም ከፍለውበታልና እሳቸውን መውቀስ ተገቢ አይመስለኝም</u>።

ወደ ኋላ ተመልሶ ከ40 ዓመታት በፊት የተደረገውን እንዳዲስ በማምጣት <u>አሁን እኛ የምናደርገው ስህተት እንዳይታይ ለመሸፈን እንደሚሞክሩ ግርግር ፈጣሪዎችና የግርግር ተጠቃሚዎች ከመሆን ይልቅ፤ አሁን እኛ ምን ማድረግ አለብን? ምንስ እያደርግን ነው?</u> ማለቱ የሚጠቅም

ይመስለኛል። ይህን ስል የወንድማችንን ተግሳጽና ምክር አቧራ አልብሸ ለማለፍ ሳይሆን፤ የቀደሙ ወላጆቻችንን ስህተት ብቻ በመጥቀስ አገር ለሚያፈርሱ፤ እምነትንና ስነ ምግባርን ለሚያቃውሱ ምንደኞች ቀዳዳ ከፋች እንዳንሆን በማሰብ ብቻ ነው።

"የገብያ ግርግር ለቀጣፊ በጀው" እንደተባለው ግርግር ፈጣሪዎችና ግርግር ተጠቃሚዎች ባመጡብን ውዝንብር፤ መከፋፈሉን በመጠቀም ነጋዴው፤ ወታደሩ፤ ሁሉ ቆቡን እየጫነ በመግባት የሚያተራምሱትን "እግዚአብሄር በቀባቸው ቄስና ጳጳስ ላይ እሱ ራሱ የቀባቸው ይፍረድባቸው እንጅ እኛ ምን ማድረግ እንችላለን" የሚሉ ሁሉ "ባሏን ያፈረች ከወንድሟ ትወልዳለች" እንደሚባለው፤ ላስመሳዮች ቄሶችና ጳጳሳት ከንቱ ክብር እየሰጡ እምነታቸውን በመልቀቅ ወደ ሌላ እምነት ለመሳብ የተጋለጡ ናቸው።

ይሂይስ አዕምሮ "በጸጸት በንዴት የምንሰራውን አጥተን ሃይማኖት መለወጥ መፍትሄ ይሆን ይመስል ማተባችንን እየበጠስን ገደል የምንገባ ሞልተናል" እንዳሉት፤ በቀላጤ ወረቀት ግዝት አንስቻለሁና በያዝከው ቀጥል በሚሉ አዲስ ተክሎች የሚበረገጉትንና ቀጠሉ ብለው የሰጡትን ትእዛዝ የሚቀበሉትም እነዚህን የመሳሰሉ ከንቱ ክብር ሰጭዎች ናቸው። እንደነዚህ ያሉትን ሰዎች እነደነ አባ ፋኑኤል የመሰሉት አዲስተክሎች የሚቃገፉትን በጭፍን ከመከተላችሁ ታገሱ። አስተውሉ፤ ይልቁንም ገስጿቸው፤ አወቅንባችሁ በሏቸው ልንላቸው ይገባናል።

ይሂይስ አዕምሮ ለጽሑፋቸው "የሃይማኖት እርጅና አያድርስ" ብለው የሰጡት ርእስ ያስደነግጣል። ይሁን እንጅ የተዋህዶ ሃይማኖት እውነት ናት። እውነት ትከሳለች እንጅ አታረጅም። የተዋህዶ ሃይማኖት እንደ አባ ፋኑኤል በመሰሉ አዲስ ተክሎች ምግባረ ብልሹነትና እውቀተ ጎደሎነት እንድታረጅ የሚደርቱባትን፤ "ኢይኩን ለርስሀት ወኢለኩነኔ አላ ለሐድሶ ነፍስ ወሥጋ ወመንፈስ" ቅ ሀ ገጽ 115 ቁ 140) የሚለውን የቅዳሴያችን መደምደሚያ አንድም ብለው የተማሩ ቀሳውስት እንደሚያነሱላት አልጠራጠርም። ያም ሆነ ይህ ይሄይስ አዕምሮ የሰጡን ተግሳጽ በያዝነው መጽሀፋችን ላይ የተመሰረተ ነው። በበኩሌ ይህን መሳይ ዓይነ ልቡና ከፋች ምክር የሚጠላ "ሰነፍን እንዳይጠላህ አትምክረው" የሚለውን ያልተረዳ አዲስ ተክል ላለመሆን "ቃለ ሕይወት ያሰማዎ" ብየ ተቀብየዋለሁ። ከዚህ ዓይነት ምክር ለማምለጥ መሞከር በራሷ ድር የተተበተበች ሸረሪት መሆን ነው እያልኩ፤ ከዚህ በታች ወደ ተዘረዘሩት 8 ነጥቦች እሻገራለሁ።

1ኛ):-"አዲስ ተክል አይሁን" 2ኛ):-በጾሙ እና በጾም ጊዜ ለምን ሆነ:- 3ኛ):-አባ ፋኑኤል 4ኛ):-ጳጳሳት እያሉ 5ኛ):- የቅስና ውግዘት 6ኛ):- የግዘት መንጭ 7ኛ):- ከኔ አመራር ውጭ 8ኛ):- የሀመረ ኖህ

# "አዲስ ተክል አይሁን"

በዘመናችን እምነታችንን እጅግ የጎዳው መንፈሳዊ መሪ "አዲስ ተክል አይሁን" የሚለውን መመሪያ ባለመከተላችን ነው። በዘመናችን ያለነው ቀሳውስትና ጳጳሳት ድካማችንና ብቃት አልባነታችን፤ በሁለት ማለትም:- ከብቶችን ለይቶ በማያውቅ ረኛና፤ በህል አዝርእት መካከል ያለውን ልዩነት መግለጽ በማይችል በከተማ አደግ ሰው መግለጽ ይቻላል።

እንኳን በእምነት፤ በስነ መለኮት፤ ታሪክ፤ በባህልና በስነ ልቡና እየተመራ ህዝብ የሚመራ ቄስ ይቅርና፤ የከብት እረኛ እንኳ የከብቶችን ብዛት ቀለምና ወዝ እስኪለማመድ ሀላፊነት አይሰጠውም። የከብቶችን ብዛት አይነትና ቁጥር የት እና እንዴት እንደሚያሳምራቸው መለማመድ አለበት።

የከብቶችን ብዛት: አይነትና ጠባያቸውን በሚገባ ያላወቀ እረኛ የጎረቤቶችን ከብት ሁሉ ሰብስቦ በበረት ከተተና ከብቶች ሲተራመሱ አደሩ። ተቀላቅለው የተወሰዱባቸው የከብቶች ባለቤትችም ሲጨነቁ አደሩ። ተቀላቅለው በገቡበት በረት ዙሪያ ያሉት ጎረቤቶችም፤ ያለወትሯቸው ከብቶች ሲታመሱ አደሩ በማለት ተነጋገሩ። በበነጋውም እረኛው፤ ከሚጠብቃቸው ከብቶች ግማሾችን ትቶ ግማሾችን ይዞ መጣ። ይህኛው በረት ጎድሎ አደረ። ያኛው በረተ ሲተራመስ ሲታወክ አደረ።

ተመልከቱ! በአይን የሚታዩ ከብቶችን ለይቶ ለመጠበቅ ለእረኛ ይህን ያህል ጥንቃቄ ከጠየቀ፤ በእምነት፤ በታሪክ፤ በባህልና በስነ ልቡና እየተመራ ህዝብ የሚመራ ቄስ ምን ያህል ጥንቃቄ

እንደሚያስፈልገው  መገመት ይቻላል።

ሌላው ምሳሌ፦ በከተማ ተወልደው ከከተማ ወጥው በማያውቁ ልጆች የተከሰተው ውዥንብር ነው። የከተማ ልጆች ስንዴ: ጤፍ: ምስር: ባቄላ: በቆሎ ፍሪያቸውን የሚያው ከገብያ እየተሸመቱ ሲመጡ ብቻ ነው። ከእለታት አንድ ቀን የተለያዩ የዘር አይነቶች ተዘርተው በበቀሉበት እርሻ መካከል ተወሰደና፤ አይነታቸውን እንዲናገር ተጠየቀ። የበቆሎውን ቡቃያ ጤፍ ነው አለ። የስንዴውን  ቡቃያ ባቄላ ነው አለ።

የከብቶችን ዓይነት እና ቁጥር እንዳላወቀው አዲስ እረኛ እና፤ የዘሮችን አይነት ለይቶ እንዳላወቀ በከተማ ተወልዶ እንዳደገ ልጅ፤ እንደ አባ ፋኑኤል ያሉ በቤተ ክርስቲያናችን የገቡ አዲስ ተክሎች ለህዝብ የሚናገሩትን ስንሰማ፤ አንድ ጊዜ የሮማ ካቶሊኩን ከፕሮቴስታንት። ሌላ ጊዞ ከኦርቶዶክስ በሌላ ጊዜ ደግሞ ባህሉን ከነገረ መለኮት፤ ተረቱን ከታሪክ ጋራ እየቀላቀሉ ሲናገሩ እንሰማለን። ውግዘትን እንደ ቀበሌ አሰራር በሌጣ ወረቀት አንስቻለሁ ያሉት ላዲስ ተክልነታቸው በቂ ማስረጃ ነው። እኒህን የመሳሰሉ ሰዎች እንዳይገቡ ነበር ቅዱሳት መጻህፍት "አዲስ ተክል አይሁን" ብለው አመራር የሰጡት።

ቅዱስ ጳውሎስ "ወኢይኩን ተክለ  ሐዲሰ  ከመ ኢይትዐበይ ወኢይደቅ ውስተ ፍትሀ ዲያብሎስ። (፩ኛ ጢ ፫፡፮) ማለትም፦  "ዲያብሎስ  ተማሪወቹን በሚነፋባቸው ወናፍ በመነፋት አብጠው እንዳይፈነዱ፤ ዲያብሎስ የሚለቅባቸውን ሥጋዊ ፍላጎት የመቋቋም አቅም የሌላቸውን ሰዎች በመንፈሳዊ ሀላፊነት አታሰማራ"።

ፍተሀ ነገስትም "ከመ ኢይደቅ ውስተ ስቃየ ሰይጣን ፤ ወይደሉ ከመ ይኩንዎ ሰማእተ በሰናይ እም አላውያነ ዚአነ በሃይማኖት  ከመ ኢይደቅ ውስተ ትእይርት ወውስተ አህባለ  ሰይጣን (ስለ ኤጲስ 5፥83) ብሎ ተናገረ። ይህም ማለት፦ "ዲያብሎስ  ተማሪወቹን በሚነፋባቸው ወናፍ በመነፋት አብጠው እንዳይፈነዱ፤ ወደ እምነቱ አመራር ገብተው ከመሰየማቸው በፊት ቢቻል ከእምነቱ ውጭ ያሉ ሰዎች በሰውነታቸው  በደግነታቸው ይመስክሩላቸው። ያ ባይሆን በእምነቱ ውስጥ ያሉ ሰዎች አንዳች ነቀፌታ የሚሰነዝሩባቸው አይሁኑ"።

አባ ፋኑኤልንና የቀድሞው ቄስ ታደሰን የመሳሰሉ አዲስ ተክሎች፤  ቄስ ከቀሰሰ፡ ጳጳስም ከጰጰሰ በኋላ የፈለገውን ስህተት ቢሰራ እንደተገልጋዩ  ምእመን አይገዘትም አይታሰርም። ናዛዥና አዛዥ ነው ብለው እንደሚገምቱም ተረዳሁ። እነዚህ ሰዎች "ወእመ ኮነ ዘሀለፈ  መዋዕለ  ነዊሃ  ወእምድህረዝ ዘከመ ድካመ ሃይማኖት አው ተሊዎ ቃል መስተቃርን  አው ተሀየየ  እምዘ ይደሉ ለዕሌሁ በምንትኒ እመዓርገ  ክህነት።  ( ፍ አ ፱፡ቁ ፪፻፹3) ብሎ  ከሚናገረው መመሪያችን ጋራ ተጋጭተዋል። ይህም ማለት፦ "ለብዙ ዘመን ባገልግሎት ላይ ቢቆይም በእምነቱ ላይ ነቀፋ እንቅፋት እና ትችት የሚያስከትል ነገር ሰርቶ ቢገኝ ከክህነት ይባረር" ነው የሚለው። አባ ፋኑኤል "ደስ ይበላችሁ ተሾምኩላችሁ" እሬሳየ ወደ ኢትዮጵያ  አይገባም" ብለው ከተናገሯቸውና ጾሙንም እንደ መጋረጃ ለመጠቀም ከመሞከር በላይ ምን እንቅፋት ይኖራል? እነዚህ ሁሉ ያልተገረዙ ንግግሮች ካዲስ ተክለነት የፈለቁ ናቸው።

## እንዲውም በጾም ጊዜ ነው መሰራት ያለበት

አባ ፋኑኤል በጾም ጊዜ መፈጸሙን ተቃውመው ግዝቱን በጻፉት ወረቀት ለማንሳት መሞከራቸው ባልዋሉበት በማያውቁት ውስጥ ገብተው መጽሀፉን ለራሳቸው ፍላጎት ጠምዝዘው ከማቅረባቸውም ባሻገር ሊቃውንቱ እና ምእመናን ከራሳቸው በላይ ከፍ አርገው የሚመለከቱትን ጵጵስናውን ከግል ፍላጎታቸው ጋራ በማያያዝ ከረግረግ ጭቃ ላይ ጥለውታል።

ይህ ምዕራፍ የሚናገረው ስለ ጾም መሆኑ እርግጥ ነው። ነገር ግን እሳቸው ባቀረቡት መንገድ ማየት ትልቅ ክህደት ነው። ምዕራፉ   "በኃይል ጩኽ፤ አትቆጠብ፤ ድምጽህን እንደመለከት አንሳ፤ ለህዝቤ መተላለፋቸውን ንገራቸው 58፥1"  እያለ ይጀምርና ፤ "የእግዚአብሄር አፍ ይህን ተናግሯል (14)  በማለት ይደመድማል።

ወንድማችን ይሄይስ አዕምሮ "ይህችን ጽሁፍ ባልጽፍ በወደድኩ ። ግን ያበጠው ይፈንዳ እንጅ እጽፋታለሁ። በስንቱ ታፍኘ እዘልቀዋለሁ" ብለው በመግቢያዋ ላይ እንደተናገሩት፤ እኛም በቀድሞው ቄስ ታደሰ ላይ ውግዘት ስናሳልፍ፤ ያበጠው ይፈንዳ በሚል እንጅ አባ ፋኑኤልን ከመሳሰሉ አዲስ ተክሎች ድጋፍ እናገኛለን በማለት አይደለም። ከአራት ጳጳሳት በቀር ቄስ መነኩሴና ጳጳስ ሁሉ እንዳትነኩት እያሉ አስፈራርተውናል። ይህን ሲሉ ሰውየው የተወቀሱበትን ነገር አልፈጸሙም ንጹህ ናቸው በማለት አይደለም።

<u>እኛም በዚህ ውስጥ ስንገባ ሰውየው የፈጸሟቸውን የስህተት አይነቶች ፈጽመን የህዝብ ውግዘት ባይደርስብንም፤ ቅስናችን እንድንፈጽም ያዘዘንን ሁሉ ፈጽመናል፤ ምንም ስህተት የለብንም፤ ከሰማይ የወረድን መላእክት ቅዱሳን ነን ብለን አይደለም።</u>

የቀድሞው ቄስ ታደሰ በህዝብ የተወቀሱበትን ጉዳይ በባህላችን በእምነታችን መሰረት ወደ ሊቃውንቱ ወደ ሽማግሌ ከማቅረብ ይልቅ ወደ ዓለማዊ አደባባይ ራሳቸው በማውጣቸው፤ ከወላጅ እናታቸው ጋርም የተስማማንበትን የሽምግልና ጥያቄ በመተላለፋቸው፤ የአባቶቻችን ቀሳውስት ስርአት በመከተል የህዝቡን የውግዘት ጩኸት ወደ መለከት ድምጽነት ለውጠነዋል።

አልገባቸውም እንጅ የውግዘቱ መሰረት የቀድሞው ቄስ ታደስ በወላጅ እናታቸው አማካይነት የቀረበላቸውን ሽምግልና ባለመቀበላቸው ውግዘቱ እንዲያውም ታሪካዊ ከዚህ ቀደም ተደርጎ በማይታወቅ ባአስገራሚ ሁኔታ የተከናወነ ነው። ይሁን እንጅ በውስጣቸው ሀሰት ሽፍጥ የተሸከሙት አዲሱ ተክል አባ ፋኑኤል፤ ህዝቡን የማያስብ የማይሰማ እንደከብትም የሚነዳ አድርገው በመገመት በራሳቸው ላይ የሚፈርድባቸውን መጽሐፍ ገልብጠው አቀረቡለት።

## <u>አባ ፋኑኤል የገለበጧቸው በጾም መደረግ ያለባቸው ጉዳዮች</u>

"የገዛ መንገድህን ከማድረግ፤ ፈቃድህንም ከመከተል ከንቱ ነገርንም ከመናገር ተከልከል"(13) የሚለውን ቃል ገልብጠው የራሳቸውን ፍላጎት በመከተል ሀሰትና አስመሳይ ነገር በመናገር በራሳቸው መንገድ ጠመዘዙት ።

"የበደልን እስራት መፍታት" ይቅርና "መላከ ኪዳን የሥራ አስፈጻሚ ናቸው" በማለት በበደል እስራት እንዲቀጥሉ ትእዛዝ ሰጡ።

"የቀንበር ጠፍር መፍታት" የሚለውን ሊፈጽሙ ቀርቶ፤ የቀንበሩን እስራት የበለጠ አከረሩት።

የተገፉትን በነጻ ትለቁ ዘንድ ነው" የሚለውን ትእዛዝ ሊፈጽሙ ቀርቶ፤ የሚሊዮን ብር ካሳ ክፍያ ፈልገው ከከሰሱት ሰው ጋራ ተሰለፉ።

"የፈረሱትን ስፍራዎች ጠጋኝ" ሊሆኑ ቀርቶ ራሳቸው የተሰራውን አፍራሽ ሆነው ቀረቡ።

"የብዙ ትውልድም መሰረት ያንጻል" የተባለውን ሊፈጽሙ ይቅርና ራሳቸው ትውልድ የሚንዱ ሆኑ። ለዚህ ሁሉ በደላቸው፤ አሁን ያለንበት ጊዜ የጌታችንና የአምላካችን ጾም በማሰብ እኛም ስለ ራሳችንን ኃጢአት ስለሀገር ብሎም ስለጠቅላላዋ ዓለም በማሰብ በጸሎትና በስግደት በምንጠመድበት ሰአት ላይ ወንድምን ለመክሰስ መነሳት አስፈላጊ አልነበረም" በማለት ሊያስተምሩን ይሞክራሉ። ጾሙንም ለሽፍጣቸው ማተልያ መጋረጃ ሊያደርጉት ደፈሩ።

<u>አባ ፋኑኤል ለፈጸሟቸው ተደራራቢ በደላቸው የዲሲን ህዝብ ይቅርታ የማይጠይቁ ከሆነ በቀድሞው ቄስ ታደሰ ላይ የወሰድነውን ርምጃ በሳቸው ላይም እንድናደርገው "ወይቁሙ ካህናቲሁ በጽድቅ" የሚለው መመሪያችን ያስገድደናል።</u>

## "<u>ጳጳሳት እያሉ</u>"

"ጳጳሳት እያሉ" ለምን የቀድሞውን ቄስ ታደሰን ቄሶች ያወግዛሉ? የሚለውን ጥያቄ የቀሳውስትን ሀላፊነት ያልተገነዘቡ ምእመናን ቢጠይቁ አይደንቅም። ይኄይስ አዕምሮ "በሃይማኖት የአመስጥሮ ስልት (mystication) ሰዎች በሰዎች ሲታለሉና ጤናማ አዕምሯቸውን በማስመስያ ሲሰለቡ ስመለከት ማዘን ብቻ ሳይሆን እጅግ እበሳጫለሁ" እንዳሉት። አባ ፋኑኤል በነቢዩ ኢሳይያስ አማካይነት

እግዚአብሄር ስለጾም ከተናገረበት ምዕራፍ ለስሜታቸው የምትስማማውን ብቻ ቀንጭበው፤ በቅዱስ አትናቴዎስ ማእረግና ልብስ አጅበው ህዝቡን ለማሳሳት አቀረቡት። ክህነት አንሰጥም እንጅ ቅስና ማውገዛችንን አለማወቃቸው ማዘን ብቻ ሳይሆን፤ በድፍረት መናገራቸው እጅግ ያበሳጫል።

"በዘመናችን ሰዎች ለራሳቸው ጥቅምና ፍላጎት ሲሉ መጽሐፍ ቅዱስን ጨምሮ ቅዱሳት መጻህፍትን በርዘውና ከልሰው በሚቃረኗቸው ሞልተው ምእመናን በጭፍን ሲያሞኙ ስናይ በሰው ልጅ የዋህነት መገረማችን ከገደቡ ያልፍብናል" እንዳሉት አባ ፋኑኤል የኢሳይያስን መጽሀፍ በርዝውና ሞልተው የራሳቸውን መንፈስ አሳዝለው ማንበብ ለማይችሉት የዋህን እናቶች በማቅረባቸው ከገደቡ አልፈዋልና ሊጠየቁበት ይገባቸዋል።

ይሄይስ አዕምሮ "በካህን ሲሆን ኃላፊነቱ ስለሚከብድ ለብዙዎቹ መሰናክል ምክንያት ይሆናልና ጠንቁ ማህበረ ሰብን እስከ ማነቃነቅ ይደርሳል" እንዳሉት፤ በቨርጅንያ ኪዳነምህረት የተከሰተው ስህተት በመንበረ ፓትርያርካችን ላይ በተቀመጡት በአቡነ ማትያስ እጅ እስከመንበረ ፓትርኩ ድረስ ዘልቆ በመግባቱ ብሄራዊ ሆነ። ባካባቢው ባሉት ሁቴሎች ውስጥ ከተለያዩ አህጉራት እየመጡ የሚሰነብቱትም ሰዎች ወደየ ሀገራቸው ይዘውት በመግባት እና፤ ራሳቸው የቀድሞው ቄስ ታደሰም ጉዳዩን ወደ ፍርድ ቤት ወደ ፖሊስ ጣቢያ ይዘውት በመሮጣቸው እጅግ ጉኖ ዓለም ዓቀፍ እየሆነ ሄዷል።

"የትዳር ነገር ይቅርና በመላእክት እንኳ እንድንፈርድ አታውቁምን በወንድሞች መካከል ሽማግሌ ሊሆን የሚችል አንድ አስተዋይ ሰው በእናንተ ዘንድ አይገኝምን?" (1ኛ ቆሮ 6፥3—6) እያለ ቅዱስ ጳውሎስ በተናገረው ክርስቲያናዊ መርሆ ጉዳዩን የሚመለከት ሁሉ፤ ቤተ ክርስቲያናችንን ከቅዱስ ጳውሎስ መርሆ ውጭ አድርጎ እንዲመለከታት አድርጓታል። ኢትዮጵያዊነታችንንም ተመልካችና ሽማግሌ አልባ አድርጎ አቅርቦታል።

እነ አባ ፋኑኤል አዲስ ተክል በመሆናቸው ቅስናችን ሽምግልናችን ባህላችን በሚሰጡን ስልጣን ሀላፊነታችንን ለመወጣት የወሰድነው አቋም መሆኑን ሊረዱት ካቅማቸው በላይ ሆነ። በዘመናችን ስህተቶች እየተደራረቡ በመከሰታቸው የነ አባ ፋኑኤል አዲስ ተክልነት ያስከተለው ውዥንብር የከበደ ቢመስለንም፤ ድሮም ቢሆን ጨለማውን ብርሃን፤ ኃጢአቱን ጽድቅ፤ እገዳን ውግዘት፤እያደረጉ በማቅረብ ህዝብ የሚያሳስቱ ሰዎች እንደነበሩ የታወቀ ነገር ነው።

ቢሆንም፤ አባ ፋኑኤል ቀሳውስት ቄስን ማገድ ማውገዝ አይችሉም የሚል ማምታቻ ብቅ ስላደረጉ ይሄይስ አዕምሮ "ያበጠው ይፈንዳ" እንዳሉት፤ እኛም በነ አባ ፋኑኤል ልብ ላይ ያበጠው የኃጢአት ቡግንጅ ይፈንዳ በማለት "ወይቁሙ ካህናቲሁ በጽድቅ ዘይደሉ" አን 5፥184) ብሎ ቅስናችን የሚፈቅድልንን መመሪያ ተንተርሰን የህዝቡን የውግዘት ድምጽ ወደ መለከት ድምጽ አሻግረነዋል።

## የቅስና ውግዘት በመመሪያችን ተደጋግሞ ተገልጿል።

ጸሎታችን ተጀምሮ እስኪያልቅ ድረስ ስለ ውግዘት ደጋግሞ ያነሳል። የውገዘት ባላቤቶች ህዝብና ቀሳውስት ናቸው እንጅ ጳጳሳት አይደሉም። ከቅዳሴያችን በፊት በምንጸልየው ኪዳን "ዘወሀብከነ በመንፈስ ንኪድ ኩሎ ኃይለ ጸላኢ ከመ ንፍታህ ዘኢይትፈታህ" እንላለን። ይህም ማለት፦ "የሰይጣንን ኃይል ለመቆጣጠር የማይፈታውን እንፈታ ዘንድ መንፈሳዊ ስልጣን ሰጠኸን። በስርዓተ ቅዳሴያችንም "ዘወሀብከነ ሥልጣነ ከመ ንኪድ ከይሴ ወአቃርብተ ወዲበ ኩሉ ኃይለ ጸላኢ" ብሎ ይደግመዋል። በዲያቆናቱ የሚቀርበው ጸሎትም "በእንተ ቀሳውስት ናስተበቁእ ከመ እግዚ ኢያሰስል እምኔሆሙ መንፈሰ ክህነት" ( 41፡ 75) የሚል ነው። የቄሱ ውግዘት ከመሬት እንዳይወድቅም "ዘአስተሀቀረ ዘንተ ቃለ ቀሲስ" ብሎ ይናገራል። እንደገና "ዘአሰርከ በምድር ይኩን እሱረ በሰማያት። ወዘፈታህከ በምድር ይኩን ፍቱሀ በሰማያት" ተብሏል። በመጨረሻም "ይኩኑ ፍቱሀነ ወግዑዛነ ኩሎሙ አግብርቲከ ወአእማቲከ በበአስማቲሆሙ" ብሎ ይዘጋዋል።

ይህን ሐዋርያዊ ግዴታ መሰረት አድርጎ ቅዱስ አትናቴዎስም፤ "ኦ ካህናት አንትሙ ውእቱ አዕይንተ እግዚአብሔር ብሩሀት ተናጸሩ በበይናቲክሙ አሀዱ ምስለ ካልዑ። ሕቱ እምውስተ ሕዝብክሙ በአበይኖ ። ኢይቁም ወኢይህበር ምስሌክሙ በጸልዮ ኢዘማዊ ወኢቀታሊ ኢሰራቂ ወኢሀሳዊ" ብሎ አስተምሮናል። አዝዞናልም። ይህም ማለት:- "እናንት የእግዚአብሄር ዓይኖች ቀሳውስት፤እግዚአብሄር

የሚወደውን ለመከተል የሚጠላውን ለመሸሽ እንድታስተውሉ የእግዚአብሔር አይኖች ናችሁ። በመጀመሪያ እርስ በርሳችሁ ተራረሙ በመካከላችሁ የሚሰርቅ የሚዘሙት የሚዋሽ የሚገድል ከናንተ ጋራ እንዲጸልይ አትፍቀዱ። "ገስጽዎ ዝልፍዎ በገሀድ" በግልጽ ዝለፉት፤ ገስጹት! (9) "መአድዎ ለዘጌገየ ከመ ይህድግ ኪያሀ ፍኖተ ወይትጋነይ ለግዚ ከመ ይስርይ ሎቱ" 10" ተልእኮውን ዘንግቶ ተቃራኒ ነገር የሰራውን ካህን ወደ እግዚአብሄር እንዲመለስ ተጽእኖ አበርቱባት" ይላል። ይህን በተግባር የማናውል ከሆነ የማንውጠውን ቁርባን መጉረስ እንደ ማለት ነው።

በሞቱና በትንሳኤው ከጌታችን ጋራ ወደ ክርስቶስ የሚመጡትን አንድ ለማድረግ ቀሳውስት ያጠምቃሉ። ሙታንን ይፈታሉ። "ከመ ንፍታህ ዘኢይትፈታህ" እያሉ የሚጸልዩትን ኪዳን በተግባር ይተረጉማሉ። "ከኃጢአት ከመርገምም ከበደልም ከክህደት ከመገዘት በሐሰት ከመማል አድነን" ብለው በሚያቀርቡት ተግሳጽ አዘል ጸሎት የህሊናቸውን ዳኝነት ይጠብቃሉ።

እንድናከናውንበት የተሰጠን የቅስና ክህነት <u>ባአንዲት ጥምቀት ባአንዲት ሃይማኖት</u> ላይ የተመሰረተ ነው። ክህነት አንዲት ናት። የምንገለገልባቸው መጻሕፍት አንድ ናቸው። ስርአት አልባ ( anarchy) ተፈጥሮ ምእመናን እንዳይበታተኑ ቀሳውስት ክህነት እንዳይሰጡ ብቻ ይታገዳሉ። የቀረውን ሲፈቱና ሲያስሩ የኖሩት ቀሳውስት ናቸው። በዚህ ኃላፊነታችን በቨርጅንያ ሀመረ ኖህ ኪዳነ ምህረት ቤተ ክርስቲያን እስራትና ፍታት የጠየቀው ችግር፤ ከህዝብ ጋራ በመተባበር የሚታሰረውን አስረን የሚፈታውን ፈተናል።

እንደሚታወቀው ከዚህ ቀደም የነበሩ ጳጳሳት መመሪያችንን ተገንዝበው ስለሚገቡ፤ በቀሳውስት የተሰነዘረውን ግዝትም ሆነ እገዳ፤ እንደ አባ ፋኑኤል በቀላጤ ወረቀት ለማንሳት ደፍረው አያውቁም። ውግዘት በሀሰትና በእውነት መካከል ያለውን እትብት የሚቆርጥ ክቡር ህዝባዊና መንፈሳዊ መሳሪያ ነው። ተንኮል በተሞላ ስህተት ውግዘት የሚሰነዝር ካለም ራሱን ይቆርጠዋል። ተወጋዥንም አውጋዥንም የሚመረምር የሚመዝን ስለሆነ በቀላጤ ማንሳት የውግዘትን ሚዛንነት ሰብሮ፤ ስለትነቱንም ዱማ አድርጎ ቤተ ክርስቲያንን ለስርአት አልበኞች እንደማጋለጥ ስለሚቆጠር በቀላጤ ወረቀት ግዝት ማንሳት ከፍተኛ ወንጀል ነው።

በህዝቡ መካክል የተከሰተውን ስህተት እግዚአብሄር በሚፈቅደው መንገድ አርሙ ተብሎ ለቀሳውስት የተሰጠውን መመሪያ በገጠር በከተማ የነበሩ አባቶቻችን ቀሳውስት ተከትለዋል። እርስ በርሳቸው እየተራረሙና በህዝባቸው መካከል የሚከሰተውን ከህዝባቸውጋራ እየተናጋገሩ የሚወገዘውን እያወገዙ የሚፈታውን እየፈቱ ኢትዮጵያን የሞራልና የስነምግባር ምንጭ አድረገዋት መኖራቸውን ታሪካችን ያረጋግጣል። ይሄይስ አዕምሮ እንደገለጹት አሰማሳይ ቀሳውስት ውግዘትን ለራሳቸው ክብርና ጥቅም ይጠቀሙበት እንደነበረ ሳንክድ፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ የቅስና አገልግሎት በሐዋርያት ስራ ምእራፍ 20 ከ ቁጥር 17 እስከ 35 በተለይም ከቁጥር 15 እስከ 19 ላይ ተመዝግቦ እንደምናነበው ቅዱስ ጳውሎስ አደራ ብሎ የሰጣቸው በነዚህ ቦታዎች ይኖሩ ለነበሩት ቀሳውስት ነው።

ይህን ሐዋርያዊ ትውፊት የተረከቡት ከተቀደሰው ጋብቻ ውጭ፤ የነበሩ እውነተኞች እንደ አባ አኖሬወስን የመሳሰሉ መነኮሳት ቢኖሩም፤ የማውገዝና የመፍታትን ስራ ይሰሩ የነበሩት ከህዝብ ጋራ ተቀላቅለው የሚኖሩ በህግ በትዳር የነበሩ ቀሳውስት ነበሩ። በቁጥር 28 ላይ ጳጳስ የሚለው ቃል የግሪክ ቃል ሲሆን ዛሬ ከተበላሸው በፊታችን ቆመው በምናያቸው አንዳንድ መነኮሳት ራስ ላይ ያለ ቢመስልም፤ ምንኩስና በትዳር ተወስኖ የሚሰጠው አገልግሎት ያላረካቸው ሰዎች የሚገቡበት ግላዊ ምርጫ ነው። ምንኩስና በመጀመሪያ ከዚህ ዓለም ምኞት ሥጋዊ ፍላጎት ሸሽቶ ራስን ለማዳን ከዓለም ራስን ቆርጦ ለመጣል የሚየደረግ ውሳኔ ነው። ምንኩስና የግል መሳሪያነቱ ከግለ ሰቡ ጋራ ተስማምቶ በምንኩስና ዘመኑ የሰበሰበው ትሩፋቱ ካዲስ ተክልነት የሚያላቅቅ ለህዝብ መጥቀም መቻሉ ሲረጋገጥ ብቻ እንጅ፤ የህዝብ መገልገያ ህዝባዊ ንብረት ሆኖ የተሰጠው ቅስና ነው።

የህጻናትን ዲቁና በዚህች ጦማር ሙሉ ምክንያቱን ለመግለጽ አይቻልም እንጅ፤ መጽሀፋችን በሚያዝዘው እውቀት ችሎታና እድሜ ቢፈቅድላቸውና መውጫና መግቢያውን ከሊቃውንት ተምረው ከተረዱ "<u>አ ዲያቆናት</u> ማህቶተ ቤተ ክርስቲያን ወላእካኒሃ ምልሁ እምውስቴታ ኢየሀሉ ተኩላ ምስለ ብግእ አንቄ ምስለ ርግብ ክርዳድ ምስለ ስርናይ" (11" በሚለው መሰረት ዲያቆናትም የማውገዝ

ስልጣ አላቸው።

ውግዘት ጥርስ የሌለው አንበሳ የሚሆነው "ወለእመሰ አሰረ ወአውገዘ ዘእንበለ ርትዕ" የሚለውን መመሪያችንን ላልተረዱ እንደ አባ ፋኑኤል ለመሳሰሉ ለአዳዲስ ተክሎች ነው። "እንዘ የሀስስ ከመ ያተክዞሙ ለሰብእ ወይፈቅድ ስህተቶሙ ወተጋንዮቶሙ ሎቱ ይኩን እሱረ ወውጉዘ እምሀበ እግዚአብሄር" ብሎ መመሪያችን በሚገልጸው መሰረት፤ ያለ በቂ ምክንያት ማውገዝ እራስን እንደሚቆርጥ፤ ያለበቂ ምክንያት ውግዘትን ማንሳትም እራስን ይበላል። በቀድሞው ቄስ ላይ የሰነዘርነው ውግዘት ተመርምሮ ስህተት ሆኖ ሲገኝ መጀመሪያ እኛ ተወግዘን ነው የታደሰ ውግዘት መነሳት ያለበት።አባ ፋኑኤል በሄዱበት መንገድ በቀላጤ ወረቀት የሚነሳ ከሆነ ለስህተቱ ሃላፊነት ማሳጣትና ቤተ ክርስቲያኒቱን መልህቅ የሌላት መርከብ ማድረግ ነው። በዚህም አባ ፋኑኤል ተጠያቂ ናቸው።

## የውግዘቱ መነሻና ሀላፊነት

ውግዘት ቅዱስ ያዕቆብ እንደተናገረው፤ "እያንዳንዳችን በራሳችን ሥጋዊ ምኞት ተስበን ስንታለል ከምንገባበት ወጥመድ ተፈንጥሮ የሚሽመቀቅብን ወጥመድ ነው። ውግዘት ማለት መለየት ነው።መለየት ማለትም ሞት ነው። ስለዚህ ውግዘት የራሳችን ህሊና የምትወልዳት የኃጢአት ልጅ ናት። የተወጋዥ የልጅ ልጅ ናት። (ያዕ 1፡4-15)"። ውግዘትን ከሚያስከትሉ ታላላቅ ኃጢአቶች አንዱና ትልቁና ትዳርን በግፍና በልብ ክፋት መፍታት ነው።

በትዳር ተወስኖ ቀርቦ በቅድስና ከመኖር የበለጠ ቅድስና ባለመኖሩ መመሪያችን "ወለእመ ተፈልጠ ቀሲስ አው ዲያቆን እም ብእሲቱ በምክንየተ ተልእኮቱ ለእግዚአብሔር ኢይደልዎ ተፈልጦ። ወእመሰ ሀደጋ ለብእሲቱ በዝንቱ ይትመተር።" ብሎ ያዝዛል። ይህም ማለት፦ እንኳን በጸብና በጭቅጭቅ ሚስቱን አሳዝኖ፤ በደሎና አስመርሮ መፍታት ይቅርና፤ መመሪያችን "ወከማሁ ለእመ አውጽአ በምክንያተ ጽሙና ወምንኩስና (አን 6 ፡226) ስለሚል፤ በትዳር ከመኖር ይልቅ በምንኩስና መኖር የበለጠ ቅዱስ ያደርጋል ብሎ በማሰብ ትዳርን መፍታት አይፈቀድም። ይህን የሚያደርግ ካህን ካገልግሎቱ መወገድ አለበት። እንደ ቀድሞው ቄስ ታደሰ ትዳርን አፍርሶ መነኮስኩ ቢል ምንኩስናው ተቀባይነት የለውም። በዚህ አይነት ምንኩስና ላይ የተመሰረተ ቅስና ላገልግሎት ሊሰለፍ መመሪያችን አይፈቅድም። "ይጽሀፉ ሎቱ በእንተ ግብሩ ወይንግርወ ወእመሰ አበየ ይረድ እመዓርጊሁ" (አን 5፡157) ባለው መመሪያችን በዚህና በሌሎችም ተደራራቢ ስህተ የቀድሞውን ቄስ ታደሰን አውግዘን የተወገዙበትን ምክንያት በጽሁፍ ለህዝብ አሳውቀን ሃላፊነቱን ወስደናል።

## ከኔ አመራር ስር ስላይደሉ ማውገዝ አይችሉም፦

አባ ፋኑኤ አሁን ከሰነዘርነው ውግዘት ጋራ ሳያነካኩ ስለ ቤተ ክርስቲያናችን መከፋፈል እና በመዋቅሩ ስር አለመሆን ትክክል አይደለም ብለው መናገራቸው ተገቢ ነው። ባዳመጥናቸውም ነበር። ገለልተኛ መሆን ለዘራፊዎች ብቻ ስለጠቀመ፤ እሳቸው ነኩት ብለን ገለልተኝነትን የምንደግፈው አይደለም። ቢቻል መከፋፈሉ የሚወገድበትን መንገድ መፈለግ የሁሉም ሃላፊነት ሊሆን ይገባል። ባይቻል ግን እምነትን ባህልን በሚያስነቅፍ አጸያፊ ባህርይ ውስጥ ያሉትን ሞራለ ቢሶች ለማስወገድ ሁላችንም ልናስብበት የሚገባ ነው።

ቆሞስ አባ መላኩ በነበሩበት ጊዜ ስለማንፈገጥ እንዴት ምን ይሉ ነበር? ምንስ ይሰብኩ ነበር? ዛሬ ሰው የሚከሱበትን ማፈንገጥ; ሬሳ ሆኘ አልገባም ብለው በሽምቱት ጳጳስና ላይ ተፈናጠው ወደ አሜሪካ ከመመለሳቸው በፊት፤ ለገለልተኝነቱ መሪው መምህሩ እሳቸው እንደነበሩ የዲሲ ህዝብ አያውቅምን? ህዝብን እንደማያስብ እንደ እንስሳ መቁጠር አይደለምን? እኔም ሆንኩ አፈንጋጮች ተብለው በአባ ፋኑኤል የተከሰሱት ቀሳውስት፤ ከራሳቸው ካባ ፋኑኤል ይልቅ ስላደጉባት ለቅድስት ቤተ ክርስቲያናቸው መከፋፈል የሚያሳስባቸው ናቸው። ገለልተኞች ነን ቢሉም እሳቸውን ከመሳሰሉ አዲስ ተክል መሪዎች አመራር ካልሆነ በቀር ከዚህ በታች የተጠቀሱትን እየተማሩ ያደጉ ስለሆኑ ከቅድስት ቤተ ክርስቲያናቸው ገለልተኛ መሆንን የሚቀበሉት አይደሉም።

ዮሐንስ አፈወርቅ "በከመ ተጋብአት ዛቲ ህብስት እንዘ ዝሩት ይእቲ ማእከለ አድባር ወአውግር ወውስተ ገዳም ወቆላት ወተጋቢአ ኮነት አሐተ ጽርስፎራ ፍጽምተ ። ወከማሁ ኪያነሂ አስተጋብአነ በመለኮ ትከ እምኩሉ ሕሊና እኩይ ዘኃጢአት ውስተ ሃይማኖትከ ፍጽምት" (ገጽ፻፶፩፡ ፺፩) እንዳለው፤ ይህም "በቆላ በደጋ በተራራ በሸለቆ የተዘራ ሰንዴ ተሰብስቦ አንዲት ህብስት እንደምትሆን እኛንም በኃጢአት በተበከለ ህሊና ከመበታተን ባንዲት እምነት ሰብስበህ አንድ አድርገን።" ማለት ነው። ከእምነቱ ጉያ እንዳንወጣ፤ እሳቸውን በመሳሰሉ አዲስ ተክሎች ወደ ተለያዩ የእምነት ድርጅቶች እንዳንበትን፤ ሲክዱ አብረናቸው እንዳንክድ እንድንጠነቀቅ ያሳስበናል።

"ቤተ ክርስቲያኗ ለረዥም ዘመናት በማህበር በዝክርና በአመት በአላት በክርስትና ያንድነትን መንፈስ በህዝቡ አዕምሮ ላይ ስትቀርጸው የኖረችውን ብሄራዊ የኢትዮጵያነትን ስሜት ከትግራይ ህዝብ አዕምሮ ጠራርጎ በጠባቡ ትግሬአዊነት ስሜት በመተካት የቤተ ክርስቲያኒቱን ይዘት እያጠበቡ ራዷን ቤተ ክርስቲያኒቱን መምታት ነው" ብለው እነ አቶ ስብሀት ነጋ በዘረጉት መርኌቸው በሚሰይሟቸው ሰዎች ምክንያት ከማእከላዊው አመራር ብንርቅም፤ ከነገረ መለኮቱ ከቀኖናውና ከጠቅላላው ምስጢረ ቤተ ክርስቲያን ተለይተናል ማለት አይደለም።

ስንኳን በቋንቋ በዜግነት በባህል በአካልና በስሜት በገጠር በከተማ ካለው ህዝባችን ልንገለል፤ በዚህ እምነት ከሚመሩ ሰዎች ሁሉ ጋራ በቋንቋ በዜግነትና በባህል ከማንመስላቸው ከኦሬንታሎች አብያተ ክርስቲያናት የተለየን ነን ብለን እናምናለን። ሊቃውንት አበውም አላስተማሩንም። የከንሳስ ኪዳነ ምህረት ቤተ ክርስቲያን ክህነታዊ መዋቅር የተመሰረተችው በአቡነ ይስሀቅና በራሴ ሲሆን፤ አቡነ ማትያስ ደግሞ በአዲስ አበባው ሆነው ሳለ ለእምነቱ ምስክርነት ሲጋበዙ የተቀበልናቸው በዚህ ምክንያት ነበር። በመቀጠልም የሚመስሉን የአኀት አብያተ ክርስቲያናት አባቶችም መጥተው እንዲመሰክሩ ያደረግነው በእምነቱ በቀኖናው አንድነት ስላለን እንጅ በነሱ አስተዳደር ስር ስለነበርን አልነበረም።

እንደ አባ ፋኑኤል ግንዛቤ ከሆነ ገለልተኝነቱ ተጠብቆ መቀየት የነበረበት እሳቸው ሊቀ ጳጳስ ሆነው እስኪመጡ ድረስ ነበር ማለት ነው። ይህስ ነጋዴነትን አያሳይምን? የነዚህን ግለሰብ ሸፍጥ ለመረዳት ይህ ብቻ አይበቃምን? በገለልተኛነታችን ማዘንና መፍትሄ መፈለግ ሲገባን፤ ስንሾምና የበለጠ ጥቅማ ጥቅም ስናገኝ ገልልተኛነትን በመንቀፍ፤ ሳይመቹን ደግሞ ገልልተኛነትን በመደገፍና የውስጡን በመዝለፍ እንደ አባ ፋኑኤል ሆኖ መገኘትን የምንጸየፈውና የምናወግዘው አስነዋሪ ባህርይ ነው። አንዳንድ ቄሶች ሰባኪዎች እንደሚያደርጉትም ከሁለቱም ሲኖዶስ ገለልተኛ መሆን ማለት፤ በየቦታው የተከሰቱትን አይነት ስህተቶችን ለመፈጸም አመች ይሆነን ዘንድ ከተመልካችና ከታዛቢ ለመደበቅ አይደለም።

በቅዳሴ ጊዜ ከፍ አድርገን በማያዝ "ሀበነ ንህበር በዘዚአከ መንፈስ ቅዱስ ወፈውሰነ በዝንቱ ጽርስፎራ" የምንልባት ህብስት መለኮት የተወሀደው ነፍስ የተለየው አማናዊ ሥጋው ነው ብለን እምነታችንን የምንገልጽባት በኦሬንታል ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ያሉትን ሁሉ ምእመናን የምንመለከትበት ናት። በጽዋዕ ማህበራት ላይም ተዘጋጅቶ የሚቀርበው ህብስት አንድነትን ህብረትን ውህደትን እያመለከተ ቅዱሱ ሰማእቱ ያለፈበትን ውጣ ወረዶችና በደማቸው ለመመስከር የከፈሉትን መስዋዕትነት ለመሳተፍ እንጅ "ዳቦሽ ባረረ ጠላሽ በቀጠነ ይቅር ይበለሽ" ለማለት አይደለም።

የቨርጂንኒያ ኪዳነ ምህረት ቤተ ክርስቲያን ምእመናን እውነተኛውን ጠበል ጸሪቅ አዘጋጅተው የረድኤቱ ተካፋይ ስላደረጉን እያመሰግን፤ በውጭ ያለው ሁሉ በተለይም ገልልተኛ ነን የምንለው ሁሉ ያለንበትን አቅጣጫ የምንቃኝበት ወቅት የደረሰ ይመስለኛል።

## የሐመር ኖኅ ኪዳነ ምህረት ምእመናን አማናዊ ረድኤት አሳተፉን።

በማቴዎስ ወንጌል "ምዕ 10፥40_42) ላይ ክርስቶስ የተናገረውን መርሆ መሰረት በማድረግ ሊቃውንት አበው እንዳስተማሩን፤ ኢትዮጵያውያን በቅዱሳን ወይም በሰማእታት ስም ጠበል ጸሪቅ አዘጋጅተው ቄሶችን ጠርተው ባርኩልን ይላሉ። ማህበሩ በጻድቃን በሰማእታት ስም ይሁን እንጅ፤ በራእየ ዮሐንስ ምዕ 7 ላይ በተገለጸው መንገድ ምእመናኑ በ12 ቁጥር ተደራጅተው፤ ነጭ ልብስ ለብሰው የዘንባባ ዝንጣፊ በእጃቸው ይዘው በግንባራቸውም ተደፍተው፤ ለእግዚአብሄር ክብር ምስጋና ውዳሴ

ኃይልም ብርታትም ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ለአምላካችን ይሁን" እያሉ የሚያመልኩት እግዚአብሄር ነው።

ለእምነት ለእውነት ለህዝብ ተጋርደው የሞቱ ቅዱሳን ሰማእታት የሚታወሱበት ሲሆን። ተልእኮውን ለሆዳቸው ገልብጠው የተሰለፉ ቀሳውስት የጠበልና የጸሪቂን ጽንሰ ሀሳብ በማበላሸታቸው እጅግ ያሳዝናል። የጸሎቱ መነሻና መድረሻም ከሰማእቱ ረድኤት እግዚአብሄር ያሳትፈን የሚል ነው። ማለትም እንደ ቅዱሱ እንደ ሰማእቱ ለእምነታችን ለስነ ምግባራችን ለመሞት ያብቃን ማለት ነው።

<u>ዳቦ ፍለጋ የገቡ አዳዲስ ተክሎች</u> "ዳቦሽ ባረረ ጠላሽ በቀጠነ ይቅር ይበልሽ" እያሉ አላማውን ያበላሹት እንጅ፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያናችን ታላላቅ ሊቃውንት ቀሳውስት ለረዥም ዘመናት በማህበርና በዝክር እያስተማሩ በህዝቡ አዕምሮ ላይ ሲቀርጹት የኖሩት፤ ለእምነት ለፍቅር ለብሄራዊ አንድነት ተላልፎ የመሞትን ስሜት ነው። የወያኔ ካድሬዎች እነ አቶ ስብሀት ነጋ፤ እነ አቶ ገብረ ኪዳን ደስታ "ቤተ ክርስቲያኗ ለረዥም ዘመናት በማህበር በዝክርና በአመት በአላት በክርስትና ያንድነትን መንፈስ በህዝቡ አዕምሮ ላይ ስትቀርጸው የኖረችውን ብሄራዊ የኢትዮጵያዊነትን ስሜት ከትግራይ ህዝብ አዕምሮ ጠራርጎ በጠባቡ ትግሬአዊነት ስሜት በመተካት የቤተ ክርስቲያኒቱን ይዘት እያጠበቡ ራሷን ቤተ ክርስቲያኒቱን መምታት ነው" ያሉትም ይህንኑ ስሜት ለመምታት ነው።

ይሄይስ አዕምሮ "ሰላሳው ቀን አልበቃ ብሎ ብዙ ተደራቢ በዓላት መኖራቸውን ታውቁ የለም? ብዙ እጅግ በጣም ብዙ የሞኝነት ስራ በአምልኮተ እግዚአብሔር ስም ከበፊቱ ጀምሮ እየተሰራ ነው" ብለዋል። እንዳሉትም፤ እንድንሳተፍ የምንመኘው ለእውነት ተላልፎ መሞትን ሳይሆን በየዝክሩ የምንበላውን ዳቦ ከሆን ይሄይስ አዕምሮ "ብዙ የሞኝነት ስራ" ያሉትን እቀበላለሁ። እንዲያሳትፈን እግዚአብሄርን የምንለምነው፤ እንደ ቅዱሳን እና እንደ ሰማእታት ለወንድም ለሃይማኖትና ለወገን ተላልፎ መሞትን ነው። ልንቃወመው የሚገባን የበዓሉ ጽንሰ ሀሳብ በሚፈተተው ህብስትና በሚቀዳው መጠጥ ላይ ተንጠልጥሎ መቅረቱን ብቻ ነው።

ለምሳሌ:- የታህሳስ ገብርኤልን የምናስታውሰው ከመላኩ ጋራ ሰለስቱ ደቂቅን ነው። ከገብርኤል በላይ የበለጠ ማስታዋስ የሚገባንም ሰለሰቱ ደቂቅን ነው። ሰለስቱ ደቂቅ እምነታቸውን ጥለው አቋማቸውን ቀይረው በህይወት ከመኖር ይልቅ በነደደ እሳት ተቃጥለው መሞትን መረጡ። "ሲሆን የምናመልከው አምላክ ከሚነደው እሳት ያድነናል። ባያድነንም እንቃጠል እንጅ አንተ ላቆምከው ለወርቁ ምስል እንደማንሰግድ እወቅ ዳን 3፥17-18) ያሉትን እናስታውሳለን። እንግዲህ በዓላት ቅዱስ ወይም ሰማእት በደሙ የሰጠውን ምስክርነት ከመንፈሳችን ጋራ እንዲዛመድ እንድናደርገው ለማሳሰብ እንጅ ህብስቱንና መጠጡን ለመካፈል አይደለም። <u>የሀመረ ኖህ ኪዳነ ምህረት ምእመናን እስከ መጨረሽ ድረስ ገፍተው ሄደው፤ እንደሌላው ህዝብ ራሳቸውን ባይታወር በማድረግ እኛ ምን አገባን ሳይሉ፤ ቆመው ሳይታዘቡ፤ በወሰዱት ርምጃ፤ ይህን አማናዊ ረድኤት እንድንካፈል ጥሪ ስላቀረቡልን ከልብ እናመስግናቸዋለን</u>። እናንተም አመስግኑልን።

ይቆየን።

**ለሌሎች ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ ጦማሮች የሚከተለዉን ድህረ-ገጽ ይመልከቱ::**

http://www.medhanialemeotcks.org/